# ኢዴአፓ-መድህን የተሻለ አማራጭ ሆኖ ለሕዝብ ይቀርባል!

**በእስካሁኑ የፖለቲካ ባህላችን ለአገራችን ችግሮች አስተማማኝ መፍትሔ መስጠት አልቻልንም፤ በእርግጥም አገራችን ሦስተኛ አማራጭ ያስፈልጋታል።**

1. ከብዙ በጐ ታሪካዊና ባህላዊ እሴቶቻችን በተቃራኒ-ኢትዮጵያዊያን እስካሁን የመቻቻል ፖለቲካ ባህል ባለቤት ለመሆን አልታደልንም። በአገራችን ጉልቶ የሚታየው የጥላቻ፣ የመጠፋፋት፣ የመናናቅና እርስ በርስ የመናቆር ፖለቲካ ሕዝባችንን በእጅጉ እንዳንገፈገፈው ይሰማናል። እርስዎ እንደ አንድ አገሩን የሚወድ ዜጋ የሰሞኑን የአሜሪካኖች ጨዋነት የተላበሰ የምርጫ ዘመቻ በመገናኛ ብዙሃን ሲመለከቱም ውስጥዎ በከፍተኛ መንፈሳዊ ቅናት እየተብከነከነ መሆኑ ይሰማናል -። ግዴለዎትም - ፓርቲያችን ኢዴአፓ-መድህን ለዚህ አይነቱ ጨዋ የፖለቲካ ባህል ፋና ወጊ ለመሆን ሦስተኛ አማራጭ ሆኖ ቀርቧል!!

2. አገራችን ኢትዮጵያ በብዙ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ውስጥ ተዘፍቃ የምትገኝ፣ በእርስ በርስ ጦርነት፣ በበሽታና በድርቅ የአለም ምሳሌ መሆኗ የሁላችንንም ሞራል የሚፈታተን ሃቅ ነው። ለእነዚህ ሁሉ በአገራችን የሚታዩ ፈርጀ ብዙ ችግሮች የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች አንዳችን ሌላችንን ብቸኛ ተጠያቂ በማድረግ ስንወቃቀስና እራሳችንን ብቸኛ የመፍትሔ ባለቤት በማድረግ ስንመፃደቅ ኖረናል። ከዚህ አይነቱ ብልሹ የፖለቲካ ባህል መማር የቻለው ኢዴአፓ-መድህን -ሁላችንም እንደ ዜጋና ህብረተሰብ በአገራችን ለሚታዩ ችግሮች የተጠያቂነት ድርሻ እንዳለብን ከማመን አልፎ ሁላችንም የምፍትሔ አካል ነን በማለት ኢዴአፓ-መድህን ሦስተኛ አማራጭ ሆኖ ቀርቧል!!

3. እስካሁን በአገራችን ለሥልጣን የበቁ የፖለቲካ ኃይሎች ለምን ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ አካሂደው ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር መፍጠር እንዳልቻሉ እራሳችንን ስንጠይቅ ኖረናል። የአገራችን ፖለቲካ ከባድ የጽንፈኝነት ስሜት የሚታይበት ከመሆኑ አንፃር በየጊዜው ለሥልጣን የበቁ ገዥዎቻችን  የጨበጡት ሥልጣን የነብር ጅራት ሆኖ - ሥልጣናቸውን ጥያቄ ውስጥ ለሚያስገባ ዴሞክራሲያዊ ሂደትና ምርጫ ተጠራጣሪና ስጉ አድርጓቸዋል። ይህ አይነቱ የገዥዎቻችን ስሜትና ስጋት ለአገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ትልቅ እንቅፋት መሆኑን የተገነዘበው ኢዴአፓ-መድህን --ገዥው ፓርቲ ወደፊት ሥልጣኑን በሕዝብ ምርጫ የሚያጣበት ሁኔታ ሲፈጠር አባላቱና ደጋፊዎቹን ከማንኛውም የበቀል እርምጃ ነፃ የሚያደርግና የወደፊት የፖለቲካ ህልውናቸውን የሚያረጋግጥ አስተማማኝ ዋስትና ከወዲሁ እንዲያገኙ ማድረግ ወቅታዊና ተገቢ መፍትሔ ነው ብሎ በማመን ኢዴአፓ-መድህን -ሦስተኛ አማራጭ ሆኖ ቀርቧል!

4. እስካሁን ድረስ ጭፍን ድጋፍና ጭፍን ተቃውሞ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ባህሪ ዋና መገለጫ መሆኑ ለሁላችንም ግልፅ ነው። ከፊሎቻችን አገሪቱ በዴሞክራሲ፣ በልማትና በእድገት እየተጥለቀለቀች እንደሆነ አድርገን በማቅረብ ሕዝቡን በአጉል ተስፋና ደስታ ለማማለል ስንሞክር፣ ከፊሎቻችን ደግሞ አገሪቱ በአፈናና በድህነት ልትወድም እንደተቃረበች አድርገን በማቅረብ ሕዝቡን  በቀቢፀ

ተስፋ ልናሸብረው ስንሞክር ይታያል። ከዚህ አይነቱ ብልሹ የፖለቲካ አስተሳሰብ እራሱን ለማራቅ የወሰነው ኢዴአፓ-መድህን በምክኒያት የመደገፍና በምክኒያት የመቃወም የፖለቲካ ባህልን በአገራችን ለማጠናከር ኢዴአፓ-መድህን ሦስተኛ አማራጭ ሆኖ ቀርቧል!

5. እስካሁን ድረስ በአገራችን በመካሄድ ላይ የሚገኘው የፖለቲካ ትግል በሥልጣን ላይ የተቀመጡ ገዥዎችን ከሥልጣን ከማውረድ አልፎ በእነሱ ምትክ ስለሚቋቋመው ስርዓት የሚጨነቅ አልሆነም። በዚህም ምክኒያት በአገራችን የተከሰቱ የለውጥ አጋጣሚዎች በሙሉ የገዥዎች ለውጥ ከመሆን አልፈው አስተማማኝ የሥርዓት ለውጥ ለመሆን አልበቁም። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ዛሬም እንደ ትናንቱ መሠረታዊ በሚባሉ ህገ-መንግሥታዊ ጉዳዮች እንኳ ገና መግባባት ላይ አልደረስንም። የልዩነት ነጥብ መሆን በማይገባቸው አገራዊ ጉዳዮች መግባባት ይቅርና - የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች አንዳችን ለሌላችን ተገቢ እውቅናና አክብሮት እንኳ ገና መስጠት አልጀመርንም። በዚህ ዓይነቱ የከረረ ልዩነት ውስጥ ሆኖ የጋራ አገርና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት እንደማይቻል የተገነዘበው ኢዴአፓ-መድህን ለአስተማማኝ ብሔራዊ መግባባት የሚያበቃን የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ መፍጠር ወቅታዊ የፖለቲካ አጀንዳ መሆኑን በማመን ኢዴአፓ-መድህን ሦስተኛ አማራጭ ሆኖ ቀርቧል!!

6. እነዚህ ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው የትግል ስልት መርሆዎቻችን በሁለት ተቀራኒና የከረረ አቅጣጫ ላይ ከቆሙት ከገዥው ፓርቲና ከሌሎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለየ ኢዴአፓ-መድህንን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሦስተኛ አማራጭነት ሚና እንዲኖረው አስችለውታል። ሦስተኛ አማራጭነታችን በእነዚህ የትግል ስልት መርሆዎቻችን ብቻም ሳይሆን በአገሪቱ ቁልፍ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥያቄዎችም ጭምር የሚገለፅ ነው።

1. ኢዴአፓ-መድህን በአሁኑ ወቅት በኢህአዴግ የሚመራ መንግሥታዊ ሥርዓት በአገራችን መኖሩን ይቀበላል። ነገር ግን በኢዴአፓ-መድህን እምነት ይህ የኢህአዴግ መንግሥት አምባገነናዊ ባህሪ ያለውና የአገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት የማይችል ነውና በሕዝብ የምርጫ ውሳኔ ከሥልጣን እንዲወርድ በሰላማዊ መንገድ ይታገላል።

2. ኢዴአፓ-መድህን በአሁኑ ወቅት በአገራችን ልናከብረውና ልንገዛበት የሚገባ ህገ-መንግሥት መኖሩን ይቀበላል። ነገር ግን ይህ ህገ-መንግሥት ለአገሪቱ አንድነትና የኢኮኖሚ እድገት የማይበጁ አንቀፆችን ያካተተ ነውና በሕዝብ ውሳኔ ሊሻሻል ይገባዋል ብሎ ይታገላል።

3. ኢዴአፓ-መድህን በአገራችን የፖለቲካ ሥልጣንን ወደታችኛው የህብረተሰብ ክፍል የሚያዳርስ የፌደራል ሥርዓት መኖሩን ይደግፋል። ነገር ግን ቋንቋንና ብሔረሰብአዊ ማንነትን ብቻ ሳይሆን - የመሬት አቀማመጥን፣ የሕዝብ ብዛትን፣ የሕዝቦች ታሪካዊ ትስስርን፣ የአስተዳደርና የልማት አመቺነትን ጭምር እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ ፌደራላዊ አደረጃጀት ለአገራችን ያስፈልጋል ብሎ ያምናል። ከዚህም በተጨማሪ ፌደራላዊ

አደረጃጀታችን ህብረብሔራዊ አደረጃጀትንና የአገር አንድነትን የሚያጠናክር፣ የእያንዳንዱን ዜጋ የተሟላ መብት መሠረት አድርጐ የቡድን መብትን ጭምር የሚያከብር እንዲሆን ኢዴአፓ-መድህን ይታገላል!!

4. ኢዴአፓ-መድህን ለአገራችን የገበያ ኢኮኖሚ አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል-፡፡ ነገር ግን ከወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ተጠናክሮ በቂ የገበያ ውድድር እስከሚፈጠር ድርስ በኢኮኖሚው ውስጥ የተገደበ የመንግሥት ተሳትፎን የሚደግፍ ሲሆን የፖለቲካ ድርጅቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኢኮኖሚው ውስጥ ያላቸውን የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ የሚያቀጭጭ ህገ ወጥ ጣልቃ ገብነት ለማስወገድ ኢዴአፓ-መድህን ይታገላል!!

5. ኢዴአፓ-መድህን መሬት ሙሉ በሙሉ የመንግሥት ይዞት መሆን አለበት ከሚለው ከገዥው ፓርቲም ሆነ፣ መሬት ሙሉ በሙሉ የግል ይዞታ መሆን አለበት ብለው ከሚያምኑ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተለየ ሦስተኛ አማራጭ አለው፡፡ በአርሶ አደሩ ሕዝብ ይዞታ ስር ያሉ የገጠር የእርሻ መሬቶችና የግለሰብ ንብረት ግንባታ የተካሄደባቸው የገጠርና የከተማ ቦታዎች የመሸጥ መለወጥ መብትን ባካተተ ሁኔታ በግል ባለቤትነት እንዲያዙ፣ አርብቶ አደሩ ህብረተሰብ የሚኖርባቸው አካባቢዎችና በጋራ ይዞታ ስር የሚገኙ የከተማ ቦታዎች በጋራ ወይንም በማህበረሰብ ባለቤትነት እንዲያዙ፣ እስካሁን ድረስ በእርሻ ጥቅም ላይ ያልዋሉና የግለሰብ ሃብት ያልተገነባባቸው የገጠርና የከተማ ቦታዎች በሂደት ወደግል ይዞታነት እስከሚሸጋገሩ ድረስ በመንግሥት ይዞታ ስር ሆነው እንዲቀጥሉ፣ በአጠቃላይም በአገራችን ሦስት ዓይነት ማለትም የግል፣ የማህበርና የመንግሥት ባለቤትነትን የሚፈቅድ የመሬት ፖሊሲ እንዲኖር ኢዴአፓ-መድህን ይታገላል!!

6. ኢዴአፓ-መድህን በአሁኑ ወቅት በአገራችን ወደ ኢኮኖሚ እድገት የሚያመሩ አበረታች የልማት እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን ይቀበላል፡፡ ነገር ግን እድገቱ የከተማ ነዋሪውንና የሸማቹን ህብረተሰብ በሕይወት የመኖር ህልውና እየተፈታተነ የመጣና በዋናነት ዝናብ ተጠቃሚ በሆነ የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚ ጥገኛ የሆነ ጊዜያዊ እድገት በመሆኑ ከፍተኛ የፍትሃዊነትና የዘላቂነት ችግር ያለበት እድገት ነው ብሎ ይምናል፡፡ ስለሆነም የሸማቹን ህብረተሰብ የኑሮ ደህንነት ጭምር ግምት ውስጥ ያስገባ፣ ግብርናና እንዱስትሪን መሪና ተመሪ የሚያደርግ ሳይሆን ለሁሉም ክፍለ ኢኮኖሚዎች ተገቢና ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሰጥ፣ አገሪቱን በከፍተኛ ፍጥነት ከግብርና ብቸኛ ጥገኝነት አላቆ መሠረታዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርን የሚያመጣ አስተማማኝ የኢኮኖሚ እድገትና ልማት እንዲመጣ ኢዴአፓ-መድህን ይታገላል!!

የኢዴአፓ-መድህን የሦስተኛ አማራጭነት አጠቃላይ ዓላማ - ከዓለም አቀፋዊ፣ አገራዊና ወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጣሚና ታዳሽ የሆነ የሊበራል ዴሞክራሲን ተግባራዊ ማድረግ ነው!! ለአዲስ የፖለቲካ ባህል መፈጠር - እንሆ የአገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች በውል የተገነዘበና መፍትሔ የሚሆን ሦስተኛ አማራጭ ይዞ ቀርቧል!!

## ኢዴአፓ-መድህን!!